# ማነው ሀገር ወዳድ?

በወሳኝ ታሪካዊ ወቅቶችና መታጠፊያዎች ላይ መጠየቅ ያለበት ጥያቄ ነው። ማነው ሀገር ወዳድ? ሀገርስ ምንድን ናት? ማናት? ማነው ኢትዮጵያዊ? ዛሬ እነዚህ ሁሉ መልስን የሚሹ ሆነው ተገኝተዋል። ኢትዮጵያን ራሷን "የፈጠራ ወሬ ናት፤ መቶ ዓመት የሞላም ታሪክ የላት፤ ኢትዮጵያዊነትም የተጫነብን መርገም ነው" የሚሉ በጥላቻ ያበዱና ለባዕድ ያደሩ ጠባቦች ፈልተዋል። ሀገራችን የልዩ ልዩ ሀይማኖት ተከታዮች የጋራ ሀገር መሆኗንም የረሱና ጽንፈኝነትን በየአቅጣጫው እያስተጋቡ ሊሸነሽኗትም የሚፈልጉ አሉ። ሌላም ሌላም።

ኢትዮጵያ ግን አንድ ናት። ሕብረ ብሔርነት ጌጧና ጥንካሬዋም ነው--ትምክህተኞችና በተለይም ጠባብ ገንጣዮችን ማቸነፍ ከቻልን። ለዘመናት ራሱን ኢትዮጵያዊ ብሎ ኢትዮጵያን ሀገሬ ብሎ ተሳስሮ የቆየም ሕዝብ አለ፡፡ ይህ የማይካድ ታሪክ ነው። በወያኔና መሰሎቹ የሚፋቅ ታሪክም አይደለም። በመሆኑም ሀገር ወዳድ ስንል ጎጥ አፍቃሪ ማለት ሳይሆን ኢትዮጵያን የሚወድ ማለታችን ነው። ማነው ታዲያ በሀቅ ሀገር ወዳድ?

የኢትዮጵያን ጥቅም ለባዕድ አሳልፎ የሰጠ ሀገር ወዳድ አይደለም። ይህም አገዛዞችን ብቻ ሳይሆን ለባዕድ ቅጥረኛ ሆነው ሀገርና ሕዝብን የሚጎዱትንም ይመለከታል። የዛሬውን ጸረ ህዝብ ካለፈው ሲያወዳድሩ አንዳንዶች ያለፈውና የወደቀው ፋሺስት ቢያንስ ሀገር ወዳድ ነበር ይላሉ። ይህ ከባድ ስህተት ነው። የሀገርን ሕዝብ ለአረመኔ ጭፍጨፋ ዳርጎ ሀገርን እወዳለሁ ማለት ዘበት ነው። ለመስኮብ ተገዢ የነበረው አገዛዝ አንድ ትውልድ በላይ መትሮና ጨፍጭፎ፤ በአጠቃላይ ሀገሪቷንም ጎድቶ ለወያኔ ሰለባ ሰጥቷታል። ሀገሩን ሳይሆን ስልጣኑን ያፈቀረ አረመኔም ተጫውቶባት ፈርጥጧል። የዚህ ስርዓት ጀሌዎችም ጥፋታቸውን ሳያምኑ በዘንድሮው የትርምስ ፖለቲካ መድረክ ላይ ሀገር ወዳድ በሉን ብለው የሚንጫጩት ሰሚ ሊያገኝ የሚገባው አይደለም። ሀገሩን የሚወድ ሕዝቧን አይጎዳምና ነው። ሀገሩን የሚወድ በሕዝብ ላይ የፈጸመውን ወንጀል አምኖ ንስሐ ይገባልና ነው።

ለሀገርና ለሕዝብ ታግተው የሚታገሉ ሀይሎችን የሚጎዳ፤ ሊያፈርስ የሚጣጣርና የሚከፋፍልም ሀገር ወዳድ አይደለም። ሚናው በተጻራሪ ነውና። ሀገሩን የሚወድ ዜጋ ለሀገር የሚታገሉትን ድርጅቶች ይረዳል እንጂ፤ እንዲጠናከሩ ይጥራል እንጂ

ሊክፋፍላቸው፤ ሊያጠቃቸው፤ ሊያጋልጣቸውና ሊበታትናቸው አይነሳም። ምንኛ ሀገሬን እወዳታለሁ ቢልም የሚታመን አይሆንም። የሀገራችንን ክንድ ያላላልና፡ እንዲዳከም ያደርጋልና። ይህ ሚና ደግሞ ለሀገርና ሕዝብ ጠላት የሚረዳ መሆኑ ግልጽ ነው። በአሁኑ ወቅት በታጋይ ድርጅቶች ላይ የተቀነባበረ አሉታዊና አፍራሽ ዘመቻ እየተካሄደ ነው። ድርጅቶችን መውቀስና በሂስም እንዲታረሙ ማድረግ ተገቢ ሆኖ ሳለ ድራሻቸውን ለማጥፋት መረባረብ ግን የተለየ ነው። ሀገር ወዳድነትን ይጻረራል። ለወያኔ ይጠቅማል። ጠበቅና ጠለቅ ያለ ምርምር  ሲደረግም ሁሉም ሳይሆኑ አብዛኞቹ አፍራሾች ደግሞ ወይ ከወያኔ ወይ ከጸረ ኢትዮጵያ ባዕድ የሚያስተሳስራቸው በገንዘብ የተጎነጎነ ገመድ አለ።

ሀገር ወዳድ ሀገሩን በጎጥ ሆነ በሀይማኖት አይከፍልም። ጭራሽ የሚታሰብ አይደለም ማለት ይቻላል። የወያኔ ቁንጮ መሪዎች ኢትዮጵያን አምርረው ስለሚጠሉ ሊገነጣጡላት ወስነው ተንቀሳቀሱ።  በህዝብ መሀልም ክፍፍልንና ብጥብጥን አነገሱ። በዚህ ርኩስ እንቃስቃሴያቸው ሌሎች አልማር አልሻሻል ያሉ ጠባቦች ሲያጅቡ ቆይተዋል። የሕዝብን ኢትዮጵያዊነት ክደው መገነጣጠልን በብሄረሰብ ሆነ በሀይማኖት ደረጃ የሚሰብኩ በምንም መመዘኛ ሀገር ወዳድ አይደሉም። ኢትዮጵያን የሚወድ ዜጋ ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የሚታገል ይሆናል። በሕዝብ መካካል ጥላቻን ሳይሆን ታሪክ የሚያውቀው ህብረትና ፍቅር እንዲጠናከርም ይጥራል ማለት ነው።

ኢትዮጵያ የሁላችን ሀገር ናት። ድሀ ሀብታም ተባልን የጋራ ሀገር አለን። በመሆኑም ነው በሀገራችን ፍትሕና ደሞክራሲ ይስፈን ስንል የምንታገለው። የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ሀገር እንዳትሆን ማለት ነው። ለዚህም ነው ሀገር ወዳድነት ደግሞ ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ መቆምን የግድ የሚለው። አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በሀገሩ የሁለተኛ ደረጃ ዜጋ ወይም ዘላለማዊ ተጨቋኝ እንዳይሆን መፈለግና እኩልነትና ዴሞክራሲ ለሚሰፍንባት ሀገርም መታገል ያስፈልጋል ማለት ነው። ኢትዮጵያ በጥቂቶች እንድትበዘብዝ የሚመኝ ሀገሩን አይወድም። ለሀገራችን ብሩህ ቀንን አይመኝላትምና።

ሀገር ወዳድነት ተግባራዊ እንጂ አፋዊ አይደለም። ሀገሬን እወዳለሁ፤ ኢትዮጵያዬ፤ ኢትዮጵያ ሀገሬ ወዘት ብለው ራሳቸውን በሰንደቅ ዓላማችን ጠቅልለው የሚጮሁ ጥቂቶች አይደሉም። ቃልና ልብ፤ ቃልና ተግባር ግን የሚገናኙ አይደሉምና ችግር አለ። በየበዓሉ ሀገሬ ብሎ የሚጮኸው ከዚህ ባሻገር ግን በትግሉ ሜዳ ከቶም የሚገኝ አይደለም። ለዘፈንና ጭፈራ አለሁ የሚለው ዜጋ ቁጥርና የተቃውሞ ሰልፍ ሲባል የሚመጣው ዜጋ ቁጥር

ተመጣጥኖም አያውቅ ማለት እንችላለን። ስንት መቶ ሺ ዜጋ ባለባት ዋሽንግተን ዲሲ የሚደረጉ የተቃውሞ ስልፎች ሺዎችን ማሰለፍ ችለዋል? በቅንጅትና ህብረት በ1997 የተሻለ ሁኔታ ቢታይም ዛሬ ያ የለም። ያውም ዜጎች በሀገር ቤት እየተጨፈጨፉ ባለበት። በጋራ በተግባር በትግል መሰለፍ ቀርቶ መከፋፈልና ስማዕትንም መሰነጣጠቁ መዝለፉ ሰፍኗል ማለት ይቻላል። የሌሎች ሀገር ዜጎች በሺዎች ቁጥር የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ብለው ሲሰለፉ ይህን በኛ በኩል እውን ለማድረግ አልታደልንም። በሀገር ቤት ሙስሊም ኢትዮጵያውያን በሺዎች ሲሰለፉ ሌሎች ዜጎች በሺዎች ሆነው አላጀቧቸውም። በባዕድ ሀገርም የሙስሊም ዜጎችን ትግል በመደገፍ ሰልፍ ሲደረግ ለምሳሌ በዚህ ላይ በመገኘት ፈንታ የወያኔን ከፋፋይ ቅስቀሳ ተከትለው “እስላሞች ተነሱ ሊያጠፉህ፤ ከጀርባቸው አጥፌዎች አሉ” ብለው መለፈፍን  መራቅን የመረጡም አሉ። ይህ ሁሉ ሀገርን መውደድ ሳይሆን ኣፋዊ ሀገር ወዳድነት ነው--በተግባር ያልታጀበ። ሀገሩን ከልቡ የሚወድ ለሀገሩ ሕይወቱን ለመሰዋት ወደ ኋላ አይልም/ አትልም።

በአሁኑ ወቅት በወያኔና በወንጀለኞች ገፋፊነት ቀደም ለሀገሩና ለሕዝብ ሕይወቱን የሰዋውን ትውልድ ማውገዝ ሰፍኗል። ያን መስዋዕትነትና ጀግንነት ማውግዝና ማክቸልቸል የአሁኑን ትውልድ የታሪክ አርአያና ምርኩዝ ለማሳጣት ነው። በዚህ ዘመቻ ግንባር ቀደም የሆኑትን ጪሂዎች ማንነት ስንመረምር ደግሞ ይህ ግልጽ ሆኖ ይገኛል። ወይ የወያኔ ደጋፊዎችና ቅጥረኞች ናቸው፤ አሊያም ደግሞ ባለፈው ጸረ ህዝብ ሽብር ዋና ተካፋይ የሆኑና ወንጀላቸውን ሊደብቁ የሚፍጨረጨሩ ናቸው። የሁሉም ተልዕኮ ግን-- ተረዱትም አልተረዱትም--ለሀገር ብሎ መሰዋት ቂልነት ነው፤ ስህተት ነው፤ ስልጡን ፖለቲካን አለማወቅ ነው ወይም በሌላ አነጋገር ፋራነት ነው በሚል ግለኝነትንና ፍርሃትን የሚሰብክ ነው። ራስክን አውጣ ሀገር ገደል ትግባ ስሜትን ሊያሰፍን ይጥራል። ይባስ ካለም ደግሞ ከሀገር ጠላት ጋር ተቃቅፈህ ሀገርን ተቀራመት የሚል ይሆናል። ለቤት፤ ለመሬት፤ ለንግድና በአጠቃላይ--ያውም ለማይሳካ-- ጥቅም በሚል ለወያኔ ማደርን ይሰብካል። እምቢኝ ለሀገሬን ይጻረራል ማለት ነው። ለዚህም ነው ያ ትውልድ ላይ የሚዘምቱ ሀገር ወዳድነትን የሚጻረሩ ሆነው የሚጋለጡት። በርግጥ የዚያን ጊዜ ትግል አይገምገም አይወቀስ የሚል ድምጻሚ የለንም። ግን በጅምላ የታገለና የተሰዋን፤ በሀገርና ህዝብ ፍቅር ተቃጥሎና ፍርሃትን አቸንፎ ሕይወቱን የሰጠን ትውልድ ማውገዝ በምንም ስሌት ሀገርን

መውደድና ለተሳካ ትግልም አዲሱን ትውልድ ማዘጋጀት አይሆንም። ለሀገር የታገሉና የወደቁትን መዘከር ለቀጥዩ ትውልድ ቀስቃሽና አስተማሪ ነው። ትውልድ የባንዳነትን ታሪክ እንዲወርስ ከተደረገና በዚህ በዚያ ወኔው ከተሰለበ ከተጠቃ ለሀገር መቆም፤ ሀገር ወዳድ መሆን ይሳነዋል። ይህ ደግሞ ለነ ወያኔና ለጸረ ኢትዮጵያ ሀይሎች ሁሉ ሲሳይ ነው። ሀገር ወዳድነትም ከሁሉ በፊትና በላይ ሀገሬ ብሎ ሞት አይፈሬ ሆኖ በተግባር መሰለፍን ይጠይቃል።

ወያኔ 22 ዓመት የጨፈርብንና ሊቀጥልብንም የቻለው በራሳችን ድክመት ነው። መከፋፈሉ የዚህ ድክመት ዋና ነጸብራቅ ነው። ሀገር ወዳድነቱም የልብ የተግባር አለመሆኑ ሌላው ነው። ከልብ ሕይወቴ ለሀገሬ ብለን ብንነሳ መለስተኛ ቅራኔዎችን መፍታትና በጋራ ለሀገር መታገል እንችላለን። በውስጣችን የሚርመሰመሱትን ጸረ ትግል ትሎችንም ማስወገድ ቀላል ይሆንልናል። ማነው ሀገር ወዳድ? ኢትዮጵያ እማማ ብሎ የሚዘፍነው ሳይሆን ለኢትዮጵያ ሊሞትላት የተነሳው ነው። ለኢትዮጵያ በሀቅ የሚታገለው ነው። ህዝብንና ድርጅቶችን የማይከፋፍለው ነው። ጸረ ወያኔው ኢትዮጵያዊ ነው።

ጸረ ወያኔ ትግላችን ይፋፋም!

ድል ለኢትዮጵያና ለሚታገሉላት ልጆቿ !!